ኪንግደም ሳውድ ዐረቢያ
በእስልምና ጉዳዮች፣ ገንዘብ ስጦታ፣
ዳእዋና መምሪያ ሚንስቴር
የህትመትና ሳይንሳዊ ምርም
ድርጅት

# የመዲና ልዕልናና የጉብኝት ስርኣቶች

አዘጋጅ


ፕሮፌሰር ሱለይማን ቢን
ሷሊሕ ቢን አብደል አዚዝ
ኢልጉስን
በኢማም ሙሐመድ ቢን
ሱኡድ እስላማዊ ዩኒቨርስቲ
ሌክቸረር


فضل المدينة وآداب الزيارة باللغة الأمهرية

በአላህ ስም እጅግ በጣም
አዛኝ በጣም ርህሩህ በሆነው።

መዲና ማለት ነብያዊ ከተማ ናት፣ እሷም የሙስጠፋ ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም የስደት አገር ነች። በሌሎች ጣባና ጦይባ በተባሉ ስያሜዎችም ትታወቃለች። አያሌ ከሆኑት የመዲና ልዕልናዎች በቀደምትነት የሚጠቀሱት የሚከተሉት ናቸው፡

1. በሷ መኖር ደግን ነገር ሁሉ የሚያጎናጽፍ መሆኑ ከነብያችን መወራቱ::
ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም እንደዚህ ብለዋል "እሚያውቁ ቢሆን ኖሮ መዲና ለነሱ ደግ ነበረች" ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል::

2. ከሰዎች እርኩስና ብልሹውን የምታስወግድ መሆኗ::
ነብያችን መዲናን አስመልክቶ በተናገሩታ ሐዲስ እንደዚህ ብለዋል፡ ኋአሷ«መዲና»ወናፍ የብረት አመድን

«ዝቃጭን»እንደሚያስወገ ድ «እርኩስና ብልሹ» ሰዎችን ታስወግዳለችቃ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

3. እምነት«ኢማን በመጨረሻ ጊዜ» ወደሷ የሚሰበሰብና የሚጠለል መሆኑ።

ኢማን ወደሷ ይከማችና ይሰባሰባል የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡ ‹እባብ «ዞሮ ዞሮ» ወደ ጎዶው ተመልሶ እንደሚጠለል ሁሉ ኢማንም «በመጨረሻ» ወደ መዲና ተብስቦ ይጠለላልቃ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል። ማንኛውም

ምእምን የሷን ትሩፋት ለማግኘት መንፈሱ መዲናን ሁልጊዜ የምትናፍቅ ሁና ይሰመዋል።

4. መዲና ከወረርሽኝና ከደጃል የተጠበቀች መሆኗ።
የአላህ መልእክተኛ እንደዚህ ብለዋል ኋበመዲና በሮች ወረርሽኝና ደጃል እንዳይገቡ የሚጠብቁ መልኣኮች ይጠበቃሉቃ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

5. መዲና ታላቅ በረከት ያላት መሆኑ፡፡
የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል ኗጌታዬ ሆይ በመካ ያደረግህውን በረከት እጥፍ በመዲና አድርግቃ ቡኽሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

6. በሷ ሲኖሩ የሚደርሱ መከራዎችን በትእግስት መቀበል «ድንቅ»ትሩፋት መሆኑ፡፡
የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል ኗአንድም ሰው የሷን የኑሮ ችግርና መከራዋን በትእግስት አይቀበልም እኔ በቂያማ«ትንሳኤ» ቀን

ምስክር ወይም ታዳጊ የምሆነው ቢሆን እንጂ.ቃ ሙስሊም ዘግበውታል።

7.መዲና«አውሬዋ አንዳይታደን፣ ዛፏ እንዳይ ቆረጥ..»እርም መደረጉዋ።
የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል ኋመዲና ከዐይርና ከሰውር መካል ያለው ክፍሏ እርም«ሐረም» ነው «በሱ» አደጋ ያደረሰ ወይም አደጋ ያደረሰን ያሰጠጋ ሰው በሱ ላይ የአላህ፣ የመልአኮችና የሰዎች በሙሉ እርግማን ይሁንቃ። ሙስሊም ዘግበውታል።

መዲና እርም የመደረጓ ሐዲስ የሚከተሉትን ነገሮች አካቷል።
በሷ አደን ማድረግ፣ ዛፎቹዋን መቁረጥ፣ ለውጊያ መሣሪያ ማንገብ እንዲሁም አደጋ ማድረስና አደጋ ያደረሰን ሰው ማስጠጋት የተከለከለ መሆኑን ያካትታል።
8. በመዲና ነዋሪዎች ላይ መጥፎ ያሰበ ሰው ታላቅ ዛቻ የተሰነዘረበት መሆኑ።
የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል "ኣማነም ሰው መዲናን በክፉ አያስብም አላህ አርስሳ በእሳት እንዲሁም ጨው በውሃ እንደሚቀልጥ ሁሉ በእሳት

የሚያቀልጠው ቢሆን እንጂ.ቃ ሙስሊም ዘግበውታል።

9. በ«መዲና»ነብያዊው መስጊድ የሚሰገድ ሶላት ብልጫ ያለው መሆን፡፡ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል ኋበዚህ በመስጊዴ የሚሰገድ አንድ ሶላት መስጂደል ሐራምን ሳይጨምር በሌላ ቦታ ከሚሰገዱ አንድ መቶ ሺህ ሶላቶች ይበልጣልቃ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

10. የተከበረው ረውዳ ልዕልና፡፡

የአላህ መልእክተኛ አንዲህ ብለዋል ኋከቤቴና ከመንበሬ«የድስኩር መድረክ» መካከል ያለው ቦታ የገነት የሆነ አጸድ ነውቃ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

በመዲና እንዲጎበኙ የተደነገጉ ቦታዎች በነብያዊዋ መዲና አንዲንሄድባቸውና እንዲንጎበኛቸው የተደነገገ«በርካታ» ቦታዎች አሉ። እነሱም፡

1. ነብያዊው መስጊድ አሱም መዲናን ለመጎብኘትና ወደሷ

ለመሳፈር ከምንነሳባቸው ቦታዎች እጅግ ታላቁ ነው:: የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል ኋወደ ሦስት መስጊዶች እንጂ ስንቅ ሰንቆ መንገድ አይወጣም:: እነሱም መስጂደል ሐራም፣ ይህ መስጊዴና መስጂደል አቅሷ ናቸውቃ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል::
የነብያዊው መስጊድ ጉብኝት ስርኣትና ደንቦች::
መዲናን ለመጎብኘት የመጣው ጎብኚ ውደ መስጊዱ ሲደርስ ቀኝ እግሩን ባመስቀደም ይግባና ለነብያችን ሶለላሁ

አለይሂ ወሰለም የማክበር ሰላምታ ያድርስ፣ ከዚያም እንዲህ ይበል አላሁመ ኢፍተሕ ሊ አብዋበ ረሕመቲክ ወዲያውንም ለመስጊዱ ክብር«ተሒየተል መስጂድ» ሁለት ረከዓ ይስገድ፡፡ ከዚያ በኋላ ለነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ሰላምታ «ወደ መቃብሩ ቦታ» ይሂድ፡፡ ፊቱን ወደ መቃብሩ አዙሮ ቂብላን በስተጀርባው አድርጎ እንዲህ ይበል፣ አሰላሙ አለይከ አዩሃነብዩ ወረሕመቱላሂ ወበረካቱህ፣ አሽሀዱ አነከ በለግተ

አሪሳላህ ወነሰሕተል ኡማህ ወጀሀድተ ሐቀ ጂሃዲህ፡፡ ከዚያም በቀኙ በኩል አንድ እርምጃ ይራመድና እንዲህ ይበል፡፡ አሰላሙ አለይክ ያ አባበክር አሲዲቅ ያኸሊፈተ ረሱሊላህ ረዲየላሁ አንከ ወጀዛከ አን ኡመቲ ሙሐመዲን ኸይራ፡፡ ከዚያም አሁንም በቀኙ በኩል አንድ እርምጃ ይራመድና እንዲህ ይበል፣ አሰላሙ አለይክ ያ ዑመር ረዲየላሁ አንከ ወጀዛከ አን ኡመቲ ሙሐመዲን ኸይራ፡፡

ድምጹን ከፍ ባለማድረግና በቦታዎች ለረዢም ጊዜ

ባለመቆም የጉበኞቱን ስርኣት መጠበቅ ይኖርበታል፡፡
ኀብኚው መላ ጊዜውን በመጠቀም በነብያዊው መስጊድ ረዥም ጊዜ መቀመጥ፣ ዱዓእ«ጸሎት»፣ ኢስተግፋር«ምህረት ጥየቃ»፣ ዚክርና ቁርኣን መቅራት ማብዛት እንዲሁም በትምህርት ቦታዎች መገኘትና ሌሎችንም መልካም ሥራዎች ማከናወን ይኖርበታል፡፡

2. የቁባእ መስጊድ፡፡

የአላህ መልእክተኛ በየሳምንቱ ቅዳሜ ቀን

አንዳንድ ጊዜ በግራቸው ሌላ ጊዜም የጭነት ከብት ተቀምጠው ወደ ቁባ መስጊድ ይሄዱና ኋወደዚህ መስጊድ -የቁባን መስጊድ ማለታቸው ነበር- ድረስ የመጣና በሱም የሰገደ ሰው ኡምራ እንዳደረገ ያህል ነው ቃ ይሉ እንደነበር በትክከለኛ የአውሪዎች ሰንሰለት አሕመድ ዘግበዋል፡፡

3- የበቂዕና የኡሑድ«ጦርነት» ሹሃዳእ«ሰምኣታት» መቃበር፡፡

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ እንደምናገኘው ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም

ወደ በቂዕ በመሄድ በዚያ ለተቀበሩ ባልደረቦቻቸው ሰላምታ ያደርሱ ነበር፡፡ እንዲሁም ቡኻሪና መስሊም በዘገቡት ሐዲስ እንደምናገኘው ከእለታት አንድ ቀን ወደ ኡሑድ ሰምኣታት «መቃብር»ሄደው ዱዓእ አድርገውላቸዋል፡፡ እነዚህ ናቸው እንግዲህ በነብያዊዋ መዲና እንዲጎበኙ የተደነገጉ ቦታዎች፡፡ ከዚህ ውጭ ያሉት «የሚጎበኙ ቦታዎች» እንዲንጎበኛቸው የሚወደድ ለመሆኑ በሃማኖቱ መመሪያ ውስጥ መረጃ አልተገኘም፡፡

ይልቁንም ሰዎች ከሃይማኖቱ ደንብ ውጭ በራሳቸው የፈጠሩት ነገር ነው። የአላህ መልእክተኛ ደግሞ በእርግጥ እንደዚህ ብለዋል።

ኋበዚህ«በትንቢት የወረደ የአላህ ህግ በሆነው»ትእዛዛችን ከሱ ያልሆነን አዲስ ነገር የፈጠረ ሰው እሱ«ፈጥሮ የሚሠራው ነገር» ተመላሽ ነውቃ«አላህ አይቀበለውም» ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል። በሌላ ዘገባ ደግሞ ኋከትእዛዛችን ውጭ የሆነን ሥራ የሠራ ሰው እሱ ተመላሽ ነውቃ

«የሚል ይገኛል» ሙስሊም ዘግበውታል፡፡ በመሆኑም ነብዩ እንደተወደደ ህጉ የጠቀመውን ነገር በመስራትና መልእክተኛው እንዲንጎበኛቸው ወደ አላዘዙት፣ እንዲሁም ሥራቸውን አላህ ይውደድላቸውና የተከበሩ ባልደረቦቻቸው ወዳልሄዱባቸው ቦታዎች ባለመሄድ ጊዜውን ተገቢ በሆነ መልኩ ፍሪያማ በሁኑ ነገሮች ሊያሳልፍ ይገባል፡፡

ማስገን ዘቢያ ለነብዩዎች

1. ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ተከታዮቻቸው የትም ቦታ ቢሆኑ ሶላትና ሰላምታ«የአላህን የአክብሮት እዝነትና የማክበር ሰላምታ» እንዲያደርሱላቸው ጠ ይቀዋል። ይህም እንደሚደርሳቸው አውርተዋል። ያም ደግሞ ወደ መቃብራቸው ከመምጣት ጋር የተያያዘ አይደለም። ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም እንዳሉት ኳመቃብሬን «በተወሰን ቀን ወይም ሣዓት በተለየ መልኩ በመጎብየት፣ መስጊድ

በገቡ ሁሉ ዚያራ በማድረግ..» አንደባእል አትውስዱት፣ ቤቶቻችሁንም መቃብሮች አታድርጉዋቸው የትም ቦታ ብትሆኑ ለኔ የአላህን የአክብሮት እዝነት ጠ ይቁልኝ ያም ከአላህ የምጠይቁልኝ የአክብሮት እዝነት ይደርሰኛልቃ በትክክለኛ የአውሪዎች ሰንሰለት አሕመድና ሌሎችም ዘግበውታል።

ይህ ከሆነ እንግዲህ በሳቸው ላይ ሶላት ሰላምታ ለማድረስ ወደ መቃብራቸው መሳፈር አያስፈልገውም።

እንዲሁም ለአላህ መልእክተኛ ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ሰለማታ አድርሱልኝ ብሎ ለሰዎች አደራ መስጠትም አልታዘዘም፡፡ ይህውም ሰለማታውን ከየትም ቦታ ቢሆን መልኣኮች ያደርሱላቸዋልና ነው፡፡ ወደ ነብያችን መቃበር በመሳፈር ትሩፋት ዙሪያ የተወሱ«የተዘገቡ» ሐዲሶች በሙሉ ትክክለኛ አይደሉም፡፡

አንዲሁም ጎብኚው መሰጊድ በገባ ቁጥር ወደ ተከበረው መቃብር መሄድ በህጉ ደንብ ውስጥ ተካቶ አልተገኘም፡፡ ሠራቸውን

አሳህ ይውድላቸውና ባልደረቦችም ያን ሲያደረጉ አልታዩም:: ይህውም ወደ መስጊድ ሲገባ የሚለውና በሶላቱ ተሸሑድ«አተሐያቱ..»ወቅ ት የሚለው ሰላምታ ወደ መቃብሩ ያለመሄድ ለነብያችን ይደርሳልና ነው::

2. ነብኘው በነብዩ ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም መሰጊድ ሚሐራቡን«የአሰጋጁ መቆሚያ»፣ መንበሩን፣ አዕማዶችን፣ በሮችን፣ አጥሮችንና መስኮቶችን በረከት ለማግኘት በመነካካት ወይም

በመሳም እንዲሁም ደግሞ ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም በተቀበሩበት ክፍል ጡዋፍ ለማድርግ «መዞር» በመሞከር ወይም አዚያ ቦታ ዱዓእ በማድረግ የማህይማንና ከህጉ ደንብ ውጭ አዲስ ነግር ፈጣሪዎች«ቢድዓ ሠሪዎች» የሚፈጽሙት ዓይነት ሥራ ከመፈጸም ሊጠነቀቅ ይገባል፡፡ ከዚያ በላይ አስከፊው ደግሞ በነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ክብር ወይም ባላቸው ታላቅ ደረጃ በመመጀንና በመሳሰሉ በጠራው የእስልምና ህግ ተካተው በማይገኙ ነገሮች

ተመርኩዞ በቢድዓ ሠሪዎች ጸሎት«ዱዓእ» ዓይነት ዱዓእ የሚያደርግ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

ከዚያ በላይ አስቀያሚውና ዘግናኙ ደግሞ ዱዓው ከአላህ መልእክተኛ መታደግን በመለመን ወይም ታላቁ አላህ እንጂ ሊያደርገው የማይችለውን ወንጀል ምህረት፣ ጭንቅን ማስወገድ፣ ጀነት መግባትና ከእሳት መዳንን በመጠየቅ እንዲሁም ከበሽታ መዳን፣ በጠላት ላይ ድል መቀዳጀት፣ ሲሳይና ልጅ፣ እንዲ ስጠ ው በመለመን የሆነ እንደሆ ነው፡፡ እነዚህና

እነሱን የመሳሰሉ ነገሮች ታላቁ አላህ ከማይምረው ከታላቁ ማጋራት«ሽርክ» ውስጥ ይካተታሉ። ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና አላህ እንዲህ ብሏል ‟አላህ በርሱ ማጋራትን በፈጽም አይምርምቃ «ሱረቱ አልኒሳእ 48» እንዲሁም እንዲህ ብሏል ‟ብታጋራ ሥራህ በእርግጥ ይታበሳልቃ «ሱረቱ አልዙመር 65»

ነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ይህን ሁሉ አስጠ ንቅቀዋል።

‟የነብያቶቻቸውን መቃብር መስገጃ «ቤተ ጸሎት» አድርገው በመጠ

ቀማቸው አይሁድና ነሳራዎችን «ክርስተያኖች» አላህ ከአዝነቱ ያርቃቸውቃ በማለትም ይህን ሥራ የሚሠሩ ሰዎችን ረግመዋል። ሐዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።

ግድ የሚሆነው ለታላቁ አላህ ሀሳብን በመጥራት «በኢኽላስ» ዱዓእ ማድረግ ነው። ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና አላህ እንዲህ ብሏል ኋሃይማኖትንም ለሱ ፍጹም አድርጋችሁ ተገዙት «ጸልዩት»ቃ «ሱረቱ አልአዕራፍ 29» እንዲሁም አንዲህ ይላል ኋእነሆ መስጊዶችም

የአላህ ብቻ ናቸው «በውስጣቸው» ከአላህ ጋራ አንድንም አትገዙቃ «ሱረቱ አልጂን 18»።

3. በበቂዕና በኡሑድ -ሥራቸውን አላህ ይውደድላቸውና- የባልደረቦችን መቃብር የሚጎበኝ ሰው መጭውን ዓለም ማስታውስና ለሚጎበኙት ክፍል ዱዓእ ምደረግ የሚሉትንና የጉብኝቱ ምክኒያት የሆኑ ነገሮችን በልቡ ማሰብ ይኖርበታል። እንዲሁም ብስጭትና ጥላቻ የሚጠ ቁሙና ሌሎች እዚያ ቦታ መስገድ፣ዱዓእ ማድረግና

ቁርኣን መቅራት
የመሳሰሉ ማጋራት
የሚሆኑ ወይም ወደሱ
የሚመሩ ነገሮችን በግልጽ
ከማሳየት መጠንቀቅ ይጠ
በቅበታል።
እንዲሁም ሻማ ማቃጠልና
ኑዛዜዎች፣ መመጀኛዎች፣
ደዓዎችና ሌላ ነገር
ያከተቱ ደብዳቤዎችን
መቃብሩ ላይ ማስቀመጥ
በጥብቅ የተከለከለ ነው።
የአላህ መልእክተኛ ሶለላሁ
አለይሂ ወሰለም እንዲህ
ብለዋል ኋንቁ አነዚያ
ከናንተ በፊት የነበሩት
የነብያቶቻቸውንና
የጻድቃኖቻቸውን
መቃብሮች መስጊዶች

አድርገዋቸው ነበር። ንቁ መቃብሮችን መስጊዶች አታደርጉ እኔ ይህን ከልክያችኋለሁቃ ሙስሊም ዘግበውታል።

የነብያችን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ውዴታ

የአብዱላህ ልጅ ሙሐመድ ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ወደ መላው የሰው ልጅ የላካቸው የአላህ መልእክተኛ ናቸው። ነብይነትና መልእክተኝነትንም በሳቸው ደምድሟል። ታላቁ አላህ እንዳለው ኋ«ሙሐመድ ሆይ» በላቸው እናንተ ሰዎች

ሆይ እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝቃ «ሱረቱ አልአዕራፍ 158»፡፡ የላካቸውም ለዓለማቱ ሁሉ እዝነት ነው፡፡ ልቅናና ሞገስ ለሱ ይሁንና«አላህ» እንዳለው ኟ«ሙሐመድ ሆይ» ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጂ አላክንህምቃ «ሱረቱ አል አንቢያእ 107»፡፡ አንዲሁም ቅኑን መንገድ እንዲመሩ፣ አንዲያበስሩና እንዲያስጠነቅቁ ነው የተላኩት፡፡ ታላቁ አላህ እንዳለው ኟአንተ ነብዩ ሆይ እኛ መስካሪ፣ አብራሪና አስፈራሪም

አድርገን ላክንህ፡፡ ወደ አላህም በፈቃዱ ጠሪ አብሪ ብርሃንም «አድርገን ላክንህ»ቃ ፡፡ «ሱረቱ አል አሕዛብ ከ45-46» ታዲያ መልእክቱን በሚገባ አድርሰዋል፡፡ ህዝቡንም መክረዋል፡፡ ያንም ለማድረግ የቁርኣንን የመመሪያ ቃለት በማሳወቅ ማስረጃዎችን አቅርበዋል፡፡

የመልእክተኛው ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ውዴታ ከእምነት ግዴታዎች እጅግ ታላቁ ነው፡፡ የሁሉም የእምነትና የሃይማኖት ሥራዎች መሰረትም ነው፡፡

በመሆኑም የሳቸውን ውዴታ ከማንኛውም ፍጠ -ር ወዴታ ማስቀደም ግዴታ ነው:: ታላቁ አላህ እንዳለው ኣአባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንዲሞቻችሁም፣ ሚስቶቻችሁም፣ ዘመዶቻችሁም፣ የሰበሰባችኋችው ሀብቶችም፣ መክሰሯን የምትፈራት ንግድም፣ የምትወዷቸው መኖሪያዎችም፣ እናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልክተኛው በርሱ መንገድም ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ እንደሆኑ አላህ ትእዛዙን

አስከሚያመጣ ድረስ ተጠ ባበቁ በላቸው:: አላህም አመጠኞች ህዝቦችን «ቅኑን መንገድ» አይመራምቃ:: «ሱረቱ አል ተውባ 24» «ነብያችን» ሶለላሁ አለይሂ ወሰለምም እንደዚህ ብለዋል ኋአንዳችሁ እኔን ከወላጁና ከልጁ ከመላ ሰዎችም አብልጦ አስካልወደደ ድረስ «እምነቱ ምሉእ የሆነ» አማኝ አይሆንምቃ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበቀወታል:: «በአንድ ሰው ላይ»የመልእክተኛው ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም

ውዴታ ትክክለኛ መሁኑንና የሚያሳድረውን ተጽእኖ ከሚያንጸባርቁ ነገሮች መካከል የሚከተሉት ይካተታሉ፡፡

1. እሳቸውን ማክበሩና ለሳቸው ታለቅ ሞገስ መስጠቱ፡፡

2. ትእዛዛቸውን መቀበሉ፣ መምሪያቸውን መከተሉና በፈለጋቸው በመጓዝ መጽናቱ፡፡

3. ያወሩትን«ሁሉ» እውነት ብሎ መቀበሉ፡፡

4. እሳቸውን መደገፉ፣ ወደ ፈለጋችው ጥናት መጥራቱ፣ እሱንም«ፈለጋቸውን» ማክበሩና

ለሱም«ለፈለጋቸው»ጥብቅና መቆሙ::

5. በሃይማኖቱ ከደንቡ ውጭ አዲስ ነገር አለመፍጠሩ::

6. በሳቸው«በነብያችን» ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ላይ የአክብሮት እዝነት ማውረድ ማብዛቱ::

7. በሳቸውም ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ወሰን አለመተላለፉ::

የባልደረቦች ልዕልና ሥራቸውን አላህ ይውደድላቸውና «የነብያችን» ባልደረቦች የህዝቡ ሁሉ በላጭና

ከሰዎችም ሁሉ ደጎቹ ናቸው። የነብዩ ባልደረቦች እንዲሆኑ አላህ የመረጣቸው ሲሆኑ በሳቸው አምነው እሳቸውንም ረድተዋል። በአላህ መንገድ እንደእንቅፋት መፈጠር፣ ችልታ፣ ችግርና ስቃይ ያሉ ነገሮችን በትእግስት አሳልፈዋል። ታድያም አላህ ሥራቸውን ወዶላቸው ጀነትን ቃል ገብቶላቸዋል። ታላቁ አላህ እንዲያለው ኋከስደተኞቹና ከረዳቶቹም ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎች እነዚያም በበጎ ሥራ የተከተሏቸው አላህ

ከነሱ ወዷል ከርሱም
ወደዋል በሥሮቻቻውም
ወንዞች የሚፈሱባቸውን
ገነቶች በውስጣቸው
ዘለዓለም ነዋሪዎች ሲሆኑ
ለነርሱ አዘጋጅቶላቸዋል
ይህ ታላቅ እድል ነውቃ
«ሱረቱ አልተውባ 100»
መልእክተኛውም እንዲህ
ብለዋል ኋከሰዎች ደጎቹ
እኔ ባለሁበት ክፍለዘመን
ያሉት ናቸው፡፡ ከዚያም
እነሱን የሚለጥቁት
ደግሞም አነዚያን
የሚለጥቁት ናቸውቃ፡፡
ቡኻሪና ሙስሊም
ዘግበውታል፡፡
ሥራቸውን አለህ
ይውደድላቸውና

ለባልደረቦች ሙስሊሞች ሊጠበወቋቸው የሚገቡ መብቶች አሏቸው:: ከነሱም መካል የሚከተሉት ይካተታሉ:: እነሱን መውደድና ሥረቸውን አላህ ይውደድ በማለት ለነሱ ዱዓእ ማድረግ::

ደግነትና ልዕልናቸውን በልብ ማመን::

ፍትሓዊ መሆናቸውን ማመን::

በሳቸው አንጻር ልበ ንጹህ መሆንና ከመካከለቸው

ስለተፈጠረው ነገር በማንኛውም መልኩ አለማውራት።
እነሱን አለመሳደብ፣ አለማንኳሰስ እንዲሁም ደረጃቸውን ዝቅ ለማድረክ አለመሞከር።

የአላህ መልእክተኛ ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ባልደረቦች ከሶዎች ሁሉ በላጮቹና ሃይማኖቱን ለኛ ያስተላለፉ ናቸውና እነሱን መሳደቡ ታላቁ አላህ ያጎናጸፋቸውን ጥራት እንዲሁም ከነርሱ መውደዱንና ከርሱ መውደዳቸውን ማስተባብለና ተጻራሪም

ይሆናል፡፡ ከዚያም አልፎ የአላህ መልእክትኛን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ማስከፋት፣ በነሱ አንጻር የሰጡትን አደራ አለምክበር፣ በነሱ አማካይነት እንጂ ያልደረሰንን ሃይማኖቱን እንዳለ ጥርጣሪ ውስጥ ማሰገባት ይሆናል፡፡

መልእክተኛው ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም በእርግጥ እንዲህ ብለዋል ኋባልደረቦችን እትሳደቡ አንዳችሁ ኡሑድ «ተራራ»ን የሚመዝን ወርቅ ምጽዋት ቢሰጥም እንኳ ከነሱ ያንዳቸውን

እፍኝ ወይም ግማሹን መድረስ አይችልምቃ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

በነሱ ወሰንን አለመተላለፍ፡፡ «በዚህ መስክ»ደህንነት የሚገኘው እነሱን በጣም ከማጋንና ከማቃለል መካከል ያለውን መሀለኛ መንገድ በመከተል ነው፡፡ የጌትነትን ባሕሪዎች ወይም የነብያትን መብቶች በመስጠት ከደረጃቸው በላይ ከፍ ማድረግ እንዲሁም በማንኳሰስና በመሳደብ

እነሱን ማቃለል ተገቢ አይደለም፡፡

የነብያችንን ሶለላሁ አለይሂ ወሰለም ቤተሰቦች መብት መጠበቅ፡፡ እነሱም የሃሺምና የአብዱልሙጠሊብ ልጆች ናቸው፡፡ በነብያችን ቤተሰቦች የምእምናን እናቶች ሚስቶቻቸውም ይካተታሉ፡፡ ነብያችን በእርግጥ እንዲህ ብለዋል ‹‹ስለቤተሰቦቸ አላህን እንዲታስታውሱ እጠይቃችኋለሁ፡፡ ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

**ከባልደረቦቻቸው ውስጥ የሆኑት ቤተሰቦቻቸው የእምነት፣ የባልደረብነትና የዝምድና መብት አላቸው:: ከባልደረቦቻቸው ውጭ የሆኑት ቤተሰቦቻቸው ደግሞ የእምነትና የዝምድና መብት አላቸው::**

**ኪንግደም ሳውድ ዐረቢያ**

**በእስልምና ጉዳዮች፣ ገንዘብ ስጦታ፣**
**ዳእዋና መምሪያ ሚንስቴር**
**የህትመትና ሳይንሳዊ ምርም**
**ድርጅት**

**መ.ሣ.ቁ.** 61843 **ኮድ** 11478
**ቴሌ.** 00966114736999
**ፋክስ** 00966114737999
**ሪያድ** info@islam.org.sa